ቁጥር/Ref.No/TI/3043/CWD/2018
Date/ቀን/:- ህዳር 05/2018 ዓ.ም.

የአካባቢ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

ኩባንያችን ጢስ እሳት ዉኃ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር በማዕከላዊ ጎንደር ዞን፣ በምዕራብ በለሳ ወረዳ እየገነባ ለሚገኘው አይሳግ መጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ከአብክመ ውሃ እና ኢነርጅ ቢሮ ጋር ውል በመውሰድ የግንባታ ስራውን እያከናወነ ሲሆን ውል ከወሰደበት የስራ ዝርዝር ውስጥ የጉልበት ስራ በዘርፉ ለተሰማራና ደረጃ - 4 እና ከዚያ በላይ WC እና GC በሆነ የንዑስ ተቋራጭ ማስራት ይፈልጋል፡፡

1. ንዑስ ተጫራቾች ለ 2018 ዓ.ም የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ሰነድ፣ የንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ የምሰክር ወረቀት፣ የተጨማሪ እሴት ታክስና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ሰርተፊኬት እንዲሁም የታክስ ክሊራንስ ማስረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
2. ንዑስ ተጫራቾቾች የመስሪያ ዋጋቸውን ሲሞሉ ለስራው የሚያስፈልግ ማንኛውም የሰው ሀይል ወጪን ያካተተ እንደሆነ ታሳቢ ማድረግ ይኖርባቸዋ፡፡
3. ንዑስ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በባህር ዳር ከተማ፣ አጼ ቲወድሮስ ክፍለ ክተማ፣ ማራኪ ቀበሌ፣ ቴዲ የአሸከርካሪዎች ማሰልጠኛ ተቋም ፊት ለፊት ከሚገኘው የኩባንያው ዋና መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 010 /የኮንትራት አስተዳደርና ገበያ ልማት መምሪያ/ በነጻ (ያለ ክፍያ) መዉሰድ ይችላሉ፡፡
4. ጨረታው ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ከህዳር 05/2018 ዓ.ም. ጀምሮና ቅዳሜን ጨምሮ ለ07 ተከታታይ የስራ ቀናት ብቻ አየር ላይ የሚቆይ ሲሆን በ7ኛው ቀን ከቀኑ 9:00 ሰዓት ጨረታው ተዘግቶ በዚሁ ቀን ከቀኑ 9:30 ሰዓት ባህር ዳር ከተማ፣ አጼ ቲወድሮስ ክፍለ ክተማ፣ ማራኪ ቀበሌ፣ ቴዲ የአሸከርካሪዎች ማሰልጠኛ ተቋም ፊት ለፊት በሚገኘው የኩባንያው ዋና መ/ቤት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎች በተገኙበት ይከፈታል፡፡
5. የጨረታው መዝጊያና መክፈቻ ቀን የስራ ቀን ካልሆነ ጨረታው በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ተዘግቶ ይከፈታል፡፡
6. ስለጨረታው በጽሁፍም ሆነ በስልክ ማብራሪያ /ክላሪፊኬሽን/ መጠየቅ ይቻላል፡፡
7. ንዑስ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለሚያቀርቡት የመስሪያ ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ 1% ተቀባይነት ያለው የጨረታ ማስከበርያ ዋስትና (Bid Bond) በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ (CPO)፣ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ተጫራቾች በጨረታ መወዳደሪያ ሰነዱ /Bid document/ መሰረት የቴክኒካል ሰነዳቸውን፣ ዋጋ ማቅረቢያቸዉን እና የጨረታ ማስከበሪያቸዉን በታሸገ ፖስታ እና የድርጂቱን ስም በማስቀመጥና ማህተም በመምታት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
9. ንዑስ ተጫራች ድርጅቶች በሚያቀርቡት የመስሪያ ዋጋ ላይ ለእያንዳንዱ ስራ ነጠላ ዋጋ እና ጠቅላላ ዋጋውን በማያሻማ ሁኔታ በትክክል በእጅ ጽሁፍ መሙላት አለባቸው፡፡

Scanned by CamScanner

10. በሚቀርበው የቴክኒካልና የመስሪያ ዋጋ ማቅረቢያ ሰነዶች ላይ የድርጅቱ ሕጋዊ ተወካይ ፊርማና የድርጅቱ ማህተም ሊይኖርበት ይገባል።
11. ንዑስ ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመስሪያ ዋጋ የግንባታ እቃዎችን ከዋናው ተቋራጭ መጋዘን ተሽከርካሪ ላይ መጫንም ሆነ ማውረድ ስራ፣ በሰው ሀይል ማጓጓዝ፣ መገንቢያ፣ የዝርጋታና የሌሎች ወጭዎችን የሚሸፍን ይሆናል። ሌሎች ከስራዎች ጋር የተያያዙ የጉልበት ወጪዎች በተሰጠው ዋጋ ላይ ተጠቃለው መቅረብ ይኖርባቸዋል።
12. የጨረታዉ አሸናፊ አሸናፊነቱ በጽሁፍ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 5 ቀናት ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ የጠቅላላ መስሪያ ዋጋዉን 10% በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ወይም 30% በኢንሹራንስ የተዘጋጀ ዋስትና የዉል ማስከበሪያ በማቅረብ ዉል የመያዝ ግዴታ ይኖርበታል።
13. ስራውን ሰርቶ የማጠናቀቂያ ጊዜ የግንባታ ቦታ ርክክብ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ2 ወር ከአስራ አምስት/15/ ቀን ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት።
14. ንዑስ ተጫራቾች በጨረታ ወቅት የሚያቀርቡት ዋጋ ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ውል እስከሚያዝበት ቀን ቢያንስ ለ30 ቀናት ፀንቶ መቆየት የሚችል መሆን አለበት።
15. ሥራውን በገባው ውል መሠረት ያላከናወነ ንዑስ ተቋራጭ ለእያንዳንዱ የዘገየበት የግንባታ ቀናት የውሉን ጠቅላላ ዋጋ 0.1% በየቀኑ በቅጣት መልክ ይከፍላል። ነገር ግን የጉዳት ካሳ ቅጣቱ ከ10% በላይ መብለጥ የለበትም።
16. ይህ የአካባቢ ግዥ ግልፅ ጨረታ የውል አካል ሆኖ ይወሰዳል።
17. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ንዑስ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግና ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል አይችሉም።
18. ጨረታው ሲከፈት የጨረታውን ሂደት ለማዛባት የሚሞክሩ ንዑስ ተጫራቾች ከጨረታው ውጭ ይሆናሉ። ለወደፊቱም ድርጅቱ በሚያደርጋቸው ሌሎች ጨረታዎች ላይ አይሳተፉም። ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናም ይወረሳል።
19. ኩባንያው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው። ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥራችን 058-220-48-26/ በፋክስ ቁጥራችን 058-220-48-30 መጠየቅ ይችላሉ።

ኩባንያዉ

Scanned by CamScanner